# የACPS Express 1/13/2023: የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (Superintendent) ፍለጋ - የዳሰሳ-ጥናት፣ እስከ ጃንዋሪ (Jan.) 15 ቀን 2023 ድረስ ክፍት-ነው

## የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (Superintendent) ፍለጋ - የዳሰሳ-ጥናት፣ እስከ ጃንዋሪ (Jan.) 15 ቀን 2023 ድረስ ክፍት-ነው



የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ባለድርሻ-አባላቶች (stakeholders) — እስከ እሁድ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 15 ቀን 2023 ድረስ — የትምህርት ቤት ስርዓታችንን ለመምራት የሚችል ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን - በተጠናከረ-ሁኔታ በመፈለግ ላይ ያላቸውን-ሃሳብ ለአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤት ቦርድ እንዲያስገቡ፣ የተራዘመ ዕድል-ሰጥቷል። የትምህርት ቤቱ ቦርዱ፤ ስለ የሚያስፈልገው የአመራርነት ባህሪያቶች እና ስለ የትምህርት ቤት ክፍላችን/division ንብረቶች እና ፈታኝና-አስቸጋሪ ሁኔታዎች፣ ከባለድርሻ-አካላቶች (stakeholders) የተገኘውን አስተያየት እየተመለከቱ ባሉበት-ጊዜ፤ ተጨማሪ ድምጾች-ለመስማት፣ የኦንላይን የዳሰሳ-ጥናቱን - እንደገና ከፍቷል። የዳሰሳ-ጥናቱ መራዘም፤ በዚህ ፍለጋ ሂደት ውስጥ ሊሰበሰብ የሚችለውን አስተያየት ሊያስፈው ይችላል።

የኦንላይን የዳሰሳ-ጥናቱን ለማጠናቀቅ፣ ከ5-10 ደቂቃዎችን ብቻ የሚወስድ እና በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ አረብኛ እና ዳሪ ቋንቋዎች - እስከ 11:59 p.m. -እሁድ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 15 ቀን 2023 ድረስ የሚገኝ-ይሆናል። ለሁሉም የ'ACPS' ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰብ አባላቶች ክፍት-የሆነ እና በዚህ-ሂደት ውስጥ ሁሉም እንዲሳተፉ ይበረታታሉ።

በፍለጋው ሂደት ላይ እንደ አማካሪ-ድርጅት/consultant ሆኖ ተሳትፎውን የጀመረው የ'McPherson & Jacobson, L.L.C Executive Recruitment and Development' ሲሆን፤ ለዚህ-የስራ ድርሻ እጩዎችን የመለየት እና የምርመራ-ምልከታ በማድረግ፣ ለትምህርት ቤት ቦርዱ እገዛ ያደርጋሉ። ከሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቡ ትርጉም-ሰጪ የሆነ አስተያየት ለማግኘት ዕድል ለመስጠት ተጨማሪ-ጊዜን አራዝሞ መስጠት ማለት፤ በኤፕሪል (April) 2023 ውስጥ - ቋሚ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (superintendent) ለመመደብ የነበረንን ግብ በጥቂቱ ፈቀቅ-እንዲል አድርጎታል። የACPS ማህበረሰባችንን ሊመራ የሚችልና ከጁላይ (July) 1 ቀን 2023 ጀምሮ ስራ-ሊጀምር የሚችል ቀጣዩን ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (superintendent) ለመምረጥ-ምልከታ በምናደርግ ጊዜ፣ አስተያየቶች መጣታጨው እንዲቀጥል የሚበረታታ እና እውቅና-የሚሰጠው ይሆናል።

ፍላጎት-ያላቸው አካላቶች፤ የስራ-ድራሻ ዝርዝር-መግለጫውን (job description) እና የማመልከቻ ሂደቱን መመልከት ይችላሉ። እንደሁልጊዜውም፤ ለጠቅላላው የACPS ማህበረሰባችን ለሚያደርጉት ቀጣይነት ያለው እርዳታ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

## ርዕሰ መምህርን - በማመስገን ሣምንት ውስጥ - ከጄንዋሪ (Jan ) 15-21 ቀን 2023 ባለው-ጊዜ ውስጥ፣ ከACPS ጋር አብራችሁ-ተካፈሉ




ግሩም የሆኑ የትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራኖችን፣ በቨርጅኒያ የርዕሰ መምህር ማመስገኛ ሣምንት በሚከበርበት ሣምንት በሆነ ከጄንዋሪ (Jan.) 15 - 21 ቀን 2023 ባለው-ጊዜ ውስጥ አብራችሁ ተካፍላችሁ አክብሩ። በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ርዕሰ መምህራኖች - በየቀኑ የሚታየው የአመራርነት ብቃት፤ ተማሪዎቻችንን በቅድሚያ ለማድረግ  እና፣ የክፍሉን-ዕቅድ በወደፊቱ እርምጃ ውስጥ ለማስፈጸም የገፋፋን ሃይል ሆኖ አገልግሎናል። ከሚገባው-በላይ ግሩም የሆኑት ርዕሰ መምህራኖቻችን፣ የተማሪዎቻችን ፍላጎቶች መሟላታቸው ለማረጋገት እርዳታን እየሰጡ፣ ከዚያ ጎን ለጎን -  የተማሪዎችን እና የሠራተኞችን ስሜት በየቀኑ የሚያነሳሱ ናቸው።  የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ከቤተሰቦች ጋር በቀልጣፋ የግንኙነት መንገድ - በመማር ሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ግንኙነት እንዲያደርጉ፣ የሚመሯቸውም ይሆናል።

“ማንም-ሰው በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ የሚረማመድ-ሰው፣ ርዕሰ መምህራኖቻችን በተማሪዎቻቸው ሕይወት ላይ የሚያደርጉትን አስተዋጽዖ መመልከት-ይችላል። ርዕሰ መምህራኖቻችንን - ለአሳዩት ትጋት፣ ቁርጠኝነት እና ስራቸው በሚደግፈው ሁኔታ አገልግሎት በመስጠት እና የACPS ማህበረሰብን-ተቆጥሮ በማያልቅ ሁኔታ በማበልጸግ ላበረከቱት-አስተዋጽዖ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፣” ብለዋል ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)።

የርዕሰ-መምህር ማመስገኛ ሣምንት - ርዕሰ መምህራኖች እንደ የትምህርት-አሰጣጥ መሪዎች በመሆን እና እንደ ዋና የትምህርት ቤቶቻቸው አስተዳደሮች በመሆን፤ የሚጫወቱትን ዋነኛ-የሆኑ ሚና እውቅና-ይሰጣል። እነርሱ ባላቸው ራዕይ/vision እና አመራር አማካኝነት፣ ርዕሰ-መምህራኖቻችን ለተማሪዎቻችን ለትምህርት አስፈላጊ-ነገሮችን እንዲያሟላ የተመቻቸና ተንከባካቢ የሆነ አዎንታዊ-የመማር አካባቢን - ጠብቆ-ለማቅረብ እርዳታ-ያደርጋሉ። በACPS ውስጥ ያሉ ርዕሰ-መምህራኖች፣ ለሁሉም ተማሪዎች መገኘት የሚችል እና አሳታፊ የሆነውን ቃል-የተገባውን - እኩልነት፣ ከፍተኛ-ጥራት ያለት ትምህርትን ለማቅረብ - የ‘2025 Strategic Plan’ን በማከናወን እርዳታም-ያደርጋሉ።

ባለሙያተኝነት ያለው ትጋትን እና ውጤታማነቶችን ለትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህራኖች በምናከብር ጊዜ፣ ሁሉም የ‘ACPS’ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና የማህበረሰብ አባላቶች - የእነዚህ ትጉሃን-ትምህርት ሰጪዎችን አስተዋጽዖዎችን እውቅና ለመስጠት-እንዲነሳሱ ይበረታታሉ። በሣምንቱ ሙሉ ያላችሁን ምስጋና -  **#ThxACPSPrincipals** በማህበራዊ-ሚዲያ ላይ በመጠቀም እና፣ በ ፌስቡክ/Facebook፣ ትዊተር/Twitter እና ኢንስተግራም/Instagram ላይ አከባበሮችን በመከተል/follow በማድረግ እየተከታተላችሁ ቆዩ።

# የጄንዋሪ (January) በአጋርነት እና በጎ-ፍቃደኝነት (Partner & Volunteer) ላይ የሚታዩ-ጉልህ ነገሮች: የአሌክሳንድርያ - የአካባቢው ዜጎች ኔትወርክ (Concerned Citizens Network)




ከምስረታ-ጊዜው ከሆነው ከ2009 ጀምሮ፤ የአሌክሳንድርያ - የአካባቢው ዜጎች ኔትወርክ (Concerned Citizens Network) (CCNA)፣ ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) የትምህርታዊ-ማህበረሰብ፤ አመኔታ-ያላቸው ወኪል-ተከራካሪዎች ሆነዋል። ድርጅቱ የተቋቋመው፤ በዋሽንግተን ፖስት (Washington Post) - የቲ.ሲ ዊሊያምስ (T.C. Williams) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የአሁኑን የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School)ን - በመተቸት-የተፃፈውን ጽሁፍ ላይ ምላሽ-ለመስጠት የተቋቋመ ነበር። 'CCNA' ያለውን ዓላማ - በትምህርት እኩልነት፣ ማህበራዊ ፍትህ-አሰጣጥ እና ጤና ላይ ያሉትን ጉዳዮች ምላሽ በመስጠት ላይ ያደረገ-ነው። ሦስት ዋና-የሆኑ ፕሮግራሞቹን በመጠቀም - እነርሱም — 'Reach and Rise for Excellence (RARE)'፣ 'Parent Engagement Workshops' እና 'Community Forums' — ከACPS ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር ለመስራት ይጠቀማል።

"ከሌሎች የማህበረሰብ-አባላት ባለድርሻ-አባላቶች ጋር እና የእኛ አጋሮች ጋር - በሚጫወቱበት የመጫወቻ-ሜዳ ደረጃ-ድረስ በመድረስ-መስራታችንን እናጸጥላለን። በአንድነት-ሆነን፣ ሁሉን ስሜታማ የሚሆንበትን አካባቢ እንፈጥራለን፤" ብለዋል የ'CCNA' ዋና ስራ አስኪያጅ እና ጡረታ-ላይ የሚገኙት ኮነሬል ጂም ፔጅ (Col. Jim Paige)።

'RARE'፤ የ'CCNA' ዋናው ፕሮግራም፤ ትኩረት የሚያደርገው - በቀለም-ትምህርት ስኬት እና ተማሪዎችን ለቨርጅኒያ 'Standards of Learning (SOL)' የውጤት-ደረጃዎች እንዲያደርጉ በማድረግ-ላይ ትኩረት ያደርጋል። ይህ የመካሪነት-ስራ (mentoring) እና የባለሙያተኝነት የመማሪያ ፕሮግራም - ከስድስት እስከ ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችን - በፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ ደረጃ (Middle)፣ በጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት እና በፓትሪክ ሄንሪ ከK-8 ትምህርት ቤት ውስጥ አገልግሎት-ይሰጣል።

RARE' - የቀለም-ትምህርት እርዳታን፤ የቤት-ስራ እርዳታን እና የኦንላይን ፕሮግራሞችን ጨምሮ - የመማሪያ-ክፍል የትምህርት አሰጣጥን ለማሳደግ እርዳታ-ይሰጣል። የጄፈርሰን ሂውስተን (Jefferson Houston) ዋና-የትምህርት ቤት ኃላፊ - ዶ/ር ጆን መኬን (Dr. John McCain) - የ'CCNA' አጋርነትን - ዋጋው ሊተመን የማይችል ነው ብለዋል።




“የ‘CCNA’ እርዳታ - ተማሪዎቻችንን፣ ወደላቀ ደረጃ በአሁኑ ጊዜ በሚገኘው ወይም በትምህርት ዓመቱ ውስጥ እንዲደርሱ የሚያበረታታ እርዳታን እየሰጠ-ባለበት ጊዜ፤ የሚገኘው ጥቅም-ከዛሬ ባለፈ-ሁኔታ ጥቅም-በማስገኘት የሚቀጥል ነው፣” ብለዋል መኬን (McCain)። “በርካታ-በሆኑ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞች (volunteers) እና የማህበረሰብ አባላቶች - ከእኛ-ጋር እየተነጋገሩ እና እየተሳተፉ በመስራታቸው ምክንያት፤ ተማሪዎቻችን ግቦችን በማስቀመጥ ላይ ዕውቀቶችን እያገኙ እና በህይወት-ጊዜያቸው የሚኖራቸውን ጸባይ ሊገነባ የሚችለውን - ዋጋ-ያላቸውን እና የሕይወት ትምህርቶችን እየተማሩ ነው።”

በ‘CCNA’ የሚሰጠው፣ የወላጅ ተሳትፎ አውደ-ጥናቶች - ልጆቻቸውን ወክለው ወደ አስተማሪዎች እና የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ወኪል-ተከራካሪያቸው-ለመሆን ቤተሰቦችን ያበረታታል። አብዛኛውን ጊዜ በማህበረሰብ አጋሮች -የቀረቡት ከዚህ በፊት የነበሩት አውደ-ጥናቶች ያካተቱት ርዕሶች፤ እንደ “የገንዘብ አያያዝ ዕቅድ-አወጣጥ/Financial Planning” በOperation Hope፣ “መሠረታዊ የሆነ ስነ-ምግባር (Basic Etiquette)” በ‘the Allen Leadership & Protocol Institute and Family Communications’ እና “መነጋገር እንችላለ?/Can We Talk?” - በ‘the Gardner Parenting Group’ ቀርቦ-ነበር።

“በዚህ ዓመት፣ የኮሌጅ ዝግጁነት ክፍል የሆነውን - ከመካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ቤተሰቦች ጋር - ለኮሌጃቸው በቅድሚያ መዘጋጀት እንዲጀምሩ ተማሪዎችን ለመርዳት - ጨምረን እንሰራለን፣” ብለዋል አስታውቀዋል የ‘CCNA’ የቦርድ ምክትል ሊቀመንበር - ብሬንዳ አዳምስ (Brenda Adams)።

በ‘CCNA’ የቀረበው - የማህበረሰብ ፎረሞች፤ የትብብር እና ከፍ-ያለ ውይይትን ያቀረበ-ሲሆን፤ ይህም በአዘጋጁ በ‘hallmarks’ የተዘጋጀ - በማህበረሰቡ ውስጥ አጋርነቶችን ለማሳደግ የተቀረጸ-ነበር።

‘CCNA’ በጄንዋሪ (Jan.) 11 ቀን 2023 ላይ - “Equity in Education, Health & Social Justice for All” በሚል-ርዕስ፤ አጠቃላይ-ስብሰባ (town hall) አዘጋጅቷል። እንግዶች-የነበሩት፤ የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፣ የአሌክሳንድርያ ከንቲባ ጀስቲን ዊልሰን (Mayor Justin Wilson)፣ እና የ‘National Association for the Advancement of Colored People (NAACP)’ ቅርንጫው ፕሬዚዳንት ዳርሊን ፍራንክሊን (Darrlynn Franklin) ተካትተው-ነበር። ተማሪዎች፤ ከሙዚቃ & ትምህርት የላቀ-ደረጃ መድረስ ፋውንዴሽን (Foundation for Advancement in Music & Education (FAME)፣ የ‘CCNA’ አጋር፤ ለዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር (Dr. Martin Luther King Jr.) መታሰቢያነት - “Lift Every Voice and Sing” የሚለውን አቅርበዋል።

እነዚህ መደበኛ ፎረሞች፤ ለዜጎች - ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እና ለማሳወቅ፣ ስሜትን ለማነሳሳት እና ኃይልና ጉልበትን ለማህበረሰቡ ለመስጠት ስልቶችን የሚቀርጽ - ግሩም የሆኑ መድረኮች ናቸው።

“የ‘CCNA’ ለACPS እና ለአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ ያለው ቁርጠኝነት - ለበርካታ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው - እውነተኛ ተፅዕኖ-ፈጣሪ ሆኗል፤” ብለዋል የ‘Advancement Via Individual Determination (AVID) District Director/College Readiness Support’ ተወካይ - ጆዲ ፒተርስ (Jodie Peters)። “ተማሪዎቻችንን የሚመስሉ፣ አሳታፊ-የሆኑ ተናጋሪዎችን ብቻ አይደለም ያቀረቡት፣ ነገር ግን ከሌሎች ካለትርፍ-የሚሰሩ ባለድርሻ-አባላቶች ጋር አጋርነትን-የፈጠሩ፤ የ ‘Alexandria Host Lions

Club'፣ 'Rotary Club'፣ 'Giving Together'፣ እና በዕምነት-ላይ መሠረት ያድረጉ ድርጅቶችን አካትቶ - ከሲቪል-ሠራተኛው ቡድኖች እና ከቤተሰቦቻችን ጋር ግንኙነቶችን ለመፍጠር አጋርነትንም-ፈጥረዋል።"




በCOVID-19 ወረርሽኝ በፈጠረው መሰናክል-ጊዜም፤ 'CCNA' በርቀት ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለማግኘት ፈጠራዊ-መንገዶችን በመጠቀም — ዛሬም ይኸው ልምድ በስራ-ላይ መዋሉ እንዲቀጥል ያስቻለውን መንገድ ተጠቅሟል፤ ብለዋል አዳምስ (Adams)። ከመማሪያ-ክፍል ባሻገረ-ሁኔታ መማር/Learning Beyond the Classroom በሚለው ተነሳሽነቱ አማካኝነት፤ 'CCNA' - ተማሪዎች በርቀት ከታሪካዊ ምስሎች ጋር ግንኙነትን በሚፈጥሩበት ጊዜ፣ እንደ 'Tuskegee Airmen'፣ 'Sioux Code Talkers' እና ሌሎችንም አካትቶ - ዓለም-አቀፍ ዕድሎችን ለማግኘት ክፍል-አድርጎላቸዋል። ሌላ የርቀት ጉብኝት - የመካከለኛ-ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎችን - ወደ ሮሳ ፓርክስ ሚውዚየም በሞትጎመሪ፣ አላባማ (Rosa Parks Museum in Montgomery, Alabama) አስተዋውቋል።

ጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት ውስጥ በሚኖረው መጪው-ዝግጅት አማካኝነት፤ የ'CCNA' የአመራርነት 101 ፎረም፤ ስለሕይወት ልምዳቸው ከተማሪዎች ጋር ለመነጋገር - የማህበረሰብ መሪዎችን በአንድነት-የሚያመጣ-ይሆናል።
ፔጅ (Paige) እንዳሉት፤ ይህ ለተማሪዎች ጥቅም-ሰጪ ብቻ ሳይሆን፣ በርካታ የስራ-መስኮችን የተለያዩ ጎዳናዎችን የሚያሳይ - ነገር-ግን በተጨማሪ "በትምህርት ስርዓታችን ውስጥ ዜጎቻችንን የስራ-ሚና የሚሰጥ ነው።"

'ACPS' የአጋርነት ወኪል-ተከራካሪ ድርጅቶች - እንደ 'CCNA' ያሉት፤ ሁሉም እንዲካተቱ፣ መረጃ-እንዲያገኙ እና እንዲሳተፉ ለማድረግ የሁሉም ሰዎች ድምጽ አስፈላጊ መሆኑን በማቅረብ-የሚረዳ ነው። ፔጅ (Paige) እንዳሉት፤ በአሁኑ-ጊዜ በጣም አስጨናቂ-የሆነው በACPS ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች እየተጋፈጡት-ያሉት፤ ከCOVID-19 ጋር በተያያዘ ያልተላቀቅነው ነገር፣ በአዕምሮ ጤና ላይ ያለው የማግለል/stigma እና ችግሩን ምላሽ-ለመስጠት የሚያስፈልገውን እርዳታ እና ተማሪዎቻችን እነርሱ-በሚገኙበት ቦታ ላይ አግኝቶ የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ በመስጠት-ላይ መሆኑን ያምናሉ። እርሳቸውን ሲገልጹ፤ 'CCNA' በቂ-ያልሆነ አገልግሎትን ያላገኙ ልጆችን በማግኘት ለመርዳት - "ከየትም-ሆናችሁ ከየት፤ የትም-ሆናችሁ የት…እኛ ሁሉንም ተማሪዎች - እናንተን ለመርዳት እዚህ እንገኛለን" በማለት በትጋት-ይሠራል።

ፒተርስ (Peters) ጨምረው-ሲናገሩ፤ "የ'CCNA' የልገሳ-ስጦታዎች እና የገንዘብ-እርዳታ ስፖንሰር-ያደረጋቸው ለበርካታ የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና ኮሌጅ የማግኘት ፕሮግራሞች - እንደ 'AVID' የመሰለው-ዓይነት - ለቀለም-ትምህርት የላቀ-ደረጃ ላይ መድረስ እና ለሕይወት ስኬት ያለውን እውነተኛ ቁርጠኝነት ያሳያል። የ'2025 Equity for All Strategic Plan' ላይ እውነተኛ-ደጋፊዎች ናቸው።"

# የአሌክሳንድርያ የስኮላርሽፕ የገንዘብ-እርዳታ (Scholarship Fund)፣ ለACPS ተመራቂዎች - ሕልማቸውን እውን-አድርጓል



የአሌክሳንድርያ የስኮላርሽፕ የገንዘብ-እርዳታ (The Scholarship Fund of Alexandria (SFA)፣ ለአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች፣ ከሁለተኛ-ደረጃ በኋላ (post-secondary) ላሏቸው ግቦች ላይ እንዲደርሱ - መንገዶችን ይፈጥራል። ይህ - ከትምህርት ቤት ክፍል/division ጋር አጋርነትን ከመጀረበት በ1986 ዓ.ም ጀምሮ - የ'SFA' ዓላማ-ሆኖ የቆየ-ነው። የ'SFA' ዓላማ፤ ለአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች - ከኮሌጅ የማማከር እርዳታ እና የገንዘብ-እርዳታ እገዛን በመስጠት ላይ አገልግሎት-ይሰጣል። የ'SFA' እርዳታዎች - ተማሪዎችን በበርካታ ከሁለተኛ-ደረጃ በኋላ (post-secondary) ያለውን ዕቅዶች ላይ - በሁለት- ወይም በአራት-ዓመት የትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ ለመማር፣ ወይም ወደ ስራ-መስክ/ቴክኒካል ፕሮግራም ለመደባለቅ - እንደየዝንባሌያቸው የሚረዱ-ነው።

"አንድ ስኮላርሽፕ (scholarship) ብቻ-ወደ ትልውድ የሚያልፍ የገንዘብ-ጥንካሬን የሚፈጥር፣ እራስን-የመቻል እና ስኬትን ለአሌክሳንድርያ ተማሪ እና ለቤተሰቦቻቸው የሚፈጥር ነው፤" ብለው አስታውሰዋል - የ'SFA' ዋና ዳይሬክተር ጃስሚን ሚሎን (Jasmine Milone)።

'SFA' በመቀጠል - ወደ ከፍተኛ-ደረጃነት ያለው የስቴት-አቀፍ ነፃ - ለፌደራል የተማሪ እርዳታ (Federal Student Aid (FAFSA) ማመልከቻ - የማጠናቀቂያ- ደረጃውን ለበርካታ ትምህርት ቤቶች - ከFAFSA ዋናው ቁልፍ አመልካች ወደ ሆነው ወደ ኮሌጅ ገብቶ-መማርን ለማጠናቀቅ አገልግሎት-መስጠቱን ይቀጥላል። ድርጅቱ፤ የገንዘብ እርዳታ አገልግሎቱን ለተማሪዎች የመስጠት-አቅሙን ያሳደገ እና፣ አሁን ከ$1 ሚሊዮን በላይ - በስኮላርሺፖስ (scholarships) በዓመታዊነት ለተማሪዎች በሁሉም አራት አመታት የኮሌጅ ጊዜ ውስጥ ይሰጣል። በዚህ ዓመት፤ ወደ 500 የሚጠጉ ተማሪዎች - በቨርጅኒያ እና በአሜሪካ ዙሪያ በ'SFA' አማካኝነት ስኮላርሽፕን በሚጠቀሙ - በበርካታ ተቋማቶች ውስጥ፤ ተማሪዎች ተመዝግበዋል።



*ከ'CCC' ጋር በአጋርነት በመስራት፤ የ'ACHS seniors' - በ'SFA' ሠራተኛ ታጅበው - ወደ 'HBCU college fair' በጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ (George Mason University) ውስጥ ጉብኝት አድረገው ነበር።*

ትምህርት-አሰጣጡ በሩን በሚከፍት ጊዜ፤ የ‘SFA’ ግቦች ዓላማ የሚያደርጉት - በኢኮኖሚ እና በዘር ፍርሃዊ-እኩነት በማጣት ላይ የሚኖሩ እንቅፋቶችን በማስወገድ፤ ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ-ጥራት ያለው የኮሌጅ ትምህርት እና በሕይወት አቅጣጫቸው ላይ ለውጥ ለማድረግ ነው።  ‘SFA’ እና የ‘ACHS’ የኮሌጅ እና የስራ-መስክ ማዕከል (College and Career Center (CCC) - ከፍተኛ-ስኬትን ለመለየት፣ ዝቅተኛ-ገቢ ያላቸውን ተማሪዎች ለብሄራዊ ስኮላርሽፖች ለሆኑት እንደ - ‘Posse Foundation’ እና ‘Questbridge scholarships’ ወደመሣሰሉት ለመለየት - በተጨማሪም አብረው-ይሰራሉ።

ሚሎን (Milone) ያለው ዕምነቶች፤ ‘SFA’ ሳይኖር - በርካታ ተማሪዎች፣ ወደ ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ትምህርት (post-secondary education) ለመጓዝ - የገንዘብ እርዳታ ማግኛ ሂደትን ለመዳሰስ እርዳታ-ስለሚያስፈልጋቸው፤ ከሚገባው በላይ አስቸጋሪ-ሁኔታ ይገጥማቸው-ነበር። የ‘ACHS’ የትምህርት ቤት ማማከሪያ (School Counseling) አስተዳዳሪ - ሮሳሊን ብሪአና ሃርዳዌ (Rosalyn Briana Hardaway) እንዳሉት፤ የ‘CCC’ ቡድን ከ‘SFA’ ጋር ያለው አጋርነት - ለተማሪዎቻችን ስኬት ወሳኝ-የሆነው ክፍል-ነው ብለዋል።

“በአንድነት-ሆነን፤ እንቅፋቶችን በማስወገድ እና ሂደቶችን በቀላሉ በማመቻቸት - አብረን እንበለጽጋለን፤” ብለዋል ሃርዳዌ (Hardaway)። “ይህን የምናደርገው ባለን ዕውቀት እና የመረጃ-ምንጮች አማካኝነት-ቢሆንም፤  ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር በተለይ የገንዘብ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው ጋር ለመስራት-አስፈላጊ የሆነው - የተአማኝነት እና እንክብካቤ-አድራጊነት ቡድን ሆኖ-መገኘት የሚያስፈልግ-ነው።

በቅድሚያ ተማሪዎችን ወደ ኮሌጅ በመሄዳው መንገድ ላይ እንዲሆኑ በሚደረገው ጥረት-ላይ፣ ‘SFA’ - የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎችን በማካተት-ያለውን አገልግሎቶች አስፋፍቷል።



በርካታዎቹ የ‘SFA’ ደጋፊዎች - ግለሰቦች፣ በርካታ የአካባቢው የንግድ-ድርጅቶች - ባለው ዓላማ ላይ ባላቸው ዕምነት መሠረት የሚረዱ ናቸው። ከ‘SFA’ ቀና-አመለካከት ካላቸው ደጋፊዎች ጋር - የACHS አሉሙኒ (alumni)፣ ለወደፊት ቲታን ትውልዶች (Titan generations) እርዳታው እንዲቀጥል ቁርጠኛ-የሆኑም ይገኙበታል። ምንም የልገሳ-ስጦታ ትንሽ-እንዳልሆነ ካለው እምነት-ጋር፣ ‘SFA’ ለጋሾች የበለጠ ምቹነት በሚሰማቸው ቦታ ለማግኘት፤ በዓመቱ-ውስጥ በሚካሄዱ በርካታ-ቁጥር ያላቸው የገንዘብ ማሰባሰቢያ-ዝግጅቶች አማካኝነት ብዙ-ዕድሎች አሉት። በእያንዳንዱ ፀደይ (spring) ወቅት ላይ፣ የማህበረሰብ አባላት - ለ‘SFA’ የገንዘብ-እርዳታን ለማሰባሰብ - በተማሪዎች እና በቤተሰቦች ህይወት ውስጥ ለውጥ-ያመጡ ተወዳጅ አስተማሪ ወይም አስተዳዳሪን በማክበር - ያሰባስባል። የድርጅቱ ትልቁ የገንዘብ-ማሰባሰቢያ - ዓመታዊው የሆነው የጋላ (gala) ዝግጅቱ ሲሆን - በዚህ ዓመት በኤፕሪል (April) 22 ተካሂዷል። በተጨማሪም፤ ከተቀባዮቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከፍተኛ-ዋጋ በመስጠት፣ በየዓመቱ ለተወሰኑ ስኮላርስፖች ላይ የገንዘብ-እርዳታ የሚሰጡ ለጋሾች-አሉ።

‘SFA’ በተጨማሪም፤ ለመግባት (admission) እና ለገንዘብ-እርዳታ ሂደቶቹ ላይ አስቸጋሪ-ሁኔታ ለገጠሟቸው ተማሪዎችም፣ እርዳታዎችን ይሰጣል። ሃርዳዌ (Hardaway) እንደገለጹት፤ “የእኛን አሉሙኒ (alumni) መርዳታቸውን በመቀጠል - ወደ መማጠናቀቂያው-መስመር እንዲደሩ-ይረዳሉ።”

ለሚሎን (Milone)፤ እንደ ‘SFA’ አዲስ ዋና ዳይሬክተርነት፤ ተማሪዎችን ወደ አስፈላጊ ወደሆነው የስኮላርስፕ እርዳታ እንዲደርሱ ለመርዳት - የግል-ሁኔታቸው፣ እርሳቸው እራሳቸው የቲታን አሉሙነስ (Titan alumnus) ሆነው - ከACPS የሚመረቁም ልጆች መኖሩ ተጨማሪ-ያደርገዋል።

“ከዛሬዎቹ ቲታኖች/Titans ጋር ስሰራ፣ የራሴን የክፍል-ጓደኞች እና የልጆቼን የክፍል ጓደኞች ፊታቸውን እመለከታለሁ፤” ብለዋል። “ግቦች እና ህልሞች ያሏቸው፤ ጠንካራ-ሠራተኞች እና ማግኘት-የሚገባቸው ተማሪዎች ናቸው። ‘SFA’ እዚህ የሚገኘው እነርሱን - ወደ ግባቸው የሚደርሱበትን ጎዳና ቀለል-ለማድረግ፣ አደናቃፊ-ነገሮች በሚገጥሟቸው ጊዜ ተመልሰው ወደ ቀና-ጎዳና እንዲመለሱ ለመርዳት እና በመጨረሻ ወደ-መጨረሻው ማጠናቀቂያ መስመር ወደሆነው - ወደ ዲግሪዎቻቸውን እና ፕሮግራሞቻቸውን ወደማጠናቀቅ እንዲደርሱ-ለመርዳት ነው።

## ACPS - ዶ/ር ኤሪን ኮርምዌል ስቶን (Dr. Erin Cromwell Stone)ን፣ እንደ የልዩ ፕሮግራሞች (Special Programs) እና ተዛማጅ-የሆኑ አገልግሎቶች ዳይሬክተር አድርጎ - እንኳን-ደህና መጡ ብሏል



ዶ/ር ኤሪን ኮርምዌል ስቶን (Dr. Erin Cromwell Stone)፣ እንደ አዲስ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የልዩ ፕሮግራሞች (special programs) እና ተዛማጅ-የሆኑ አገልግሎቶች ዳይሬክተር ሆነው ተመርጠዋል። ዶ/ር ስቶን (Dr. Stone)፣ ዋና ዳይሬክተርን - ዕቅድ-በማውጣት፣ በበልዩ ትምህርት (special education) አገልግሎቶች ክፍል ውስጥ የአስተዳደር እና ዳይሬክተርነት ስራ ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኝ ተማሪ (students with disabilities) በከተማ-አቀፍ ፕሮግራሞች ውስጥ የመስጠት-ኃላፊነት ላይ እርዳታ ይሰጣሉ። ይህን አዲስ የስራ-ድራሻ በጄንዋሪ (Jan.) 3 ቀን 2023 ላይ በመውሰድ፤ ዶ/ር ስቶን (Dr. Stone) - ተዛማጅ አገልግሎቶችን  - በኦኩፔሽናል ቴራፒ (occupational therapy)፣ በፊዚካል ቴራፒ (physical therapy)፣ በኦዲዮሎጂ (audiology) ወይም መለመድ-ያለባቸው የአካላዊ-ብቃት ትምህርት (adapted physical education) ላይ አገልግሎት በመስጠት-የተመደቡትንም - የመመሪያው ሠራተኞችን የመቆጣጠር ስራን ይሰራሉ።

“ኤሪን (Erin)፣ ያላቸውን የእውቀት ሃብት እና ተሞክሮ - ወደ አዲሱ የስራ-ድርሻ ወደሆነው፣ የልዩ ፕሮግራሞች እና ተዛማጅ-የሆኑ አገልግሎቶች (special programs and related services) ዳይሬክተርነት የሚያመጡ-ይሆናል፤” ብለዋል ቴሪ ዌርነር (Terry Werner) - በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ የትምህርት-አሰጣጥ ዋና ዳይሬክተር። “ከACPS ጋር በነበራቸው 12 በላይ በሆኑ ዓመታት ውስጥ፣ በክፍሉ ዙሪያ ለሚገኙ ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች - ዋነኛ አገልግልቶችን በመስጠት የቡድን-መሪነት ላይ ዋነኛ-የሆነውን ክፍል ወስደው የነበሩ-ናቸው። በርካታ-አስቸጋሪ-ሁኔታዎች በበርካታ አካባቢዎች ውስጥ ለገጠሟቸው ተማሪዎች - ተጨማሪ ግንባታ እና የተስፋፉ-የፕሮግራም አሰጣጥ በመስጠት ለመምራት፣ በዚህ አዲስ የስራ-ድራሻ ውስጥ - ኤሪን (Erin) -መሪነቱን በመውሰዳቸው፣ አስደስቶናል።”

ዶ/ር ስቶን (Dr. Stone)፣ በመጀመሪያ ACPS የተቀላቀሉት በ2010 ነው፤ እና በቅርብ-ጊዜ በከተማ-አቀፍ ፕሮግራሞች እና የባህሪይ አገልግሎቶች ውስጥ እንደ ረዳት ዳይሬክተር ሆነው አገልግለዋል። ከዚህ-ቀደም፤ ለትምህርት ቤት ክፍሉ/division፣ እንደ ኦቲዝም (autism) እና የባህሪይ አገልግሎት ፕሮግራም አስተባባሪ፣ የኦቲዝም (autism) ፕሮግራም አስተባባሪ፣ እና እንደ የቦርድ-ፈቃድ ያለው የባህሪይ ተንታኔና ግምገማ-ሰጪ ሆነው አገልግለዋል።

ወደ ACPS ከመቀላቀላቸው በፊት - ዶ/ር ስቶን (Dr. Stone) - ሁለቱም በኑው ዮርክ፣ ኑው ዮርክ (New York, New York) ውስጥ በሚገኙት፤ በማይልስቶን (Milestone) ትምህርት ቤት ውስጥ - ለልጅ እድገት (Child Development) ጎን-ለጎን በሆነ — እንደ የክንውኖች ዳይሬክተር በሃኖቨር ፕሌስ የልጅ እንክብካቤ (Hanover Place Child Care) ውስጥ፣ የትምህርት አሰጣጥ ዳይሬክተር/ክሊኒካል ዳይሬክተር ሆነው-አገልግለዋል። እንደ የፕሮግራም አማካሪ፣ የትምህርት ቤት የስነ-ልቦና ባለሞያ (psychologist)፣ የስነ-ልቦና ግምገማ አድራጊ እና የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ ሆነው በኑው-ዮርክ ከተማ (New York City) ውስጥም-ሰርተዋል። በትምህርት ላይ ያላቸው የስራ-ድርሻ የጀመረው በ1993 በታምፓ ፍሎሪዳ (Tampa, Florida) ውስጥ - እንደ የስሜታዊነት እክሎች ላሏቸው ተማሪዎች አስተማሪ በመሆን ነበር።

ከK-12 ትምህርት ውስጥ ባላቸው ስራ ላይ -በተጨማሪም፤ ዶ/ር ስቶን ( Dr. Stone) - እንደ አጀሰንት ፕሮፌሰር (adjunct professor) በመሆን - የተመራቂነት (graduate) ደረጃ ኮርሶችን፣ በኤንዲኮት ኮሌጅ - በቢቨርሊ - ማሳቹሴትስ (Beverly, Massachusetts)፤ በጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ - በፌርፋክስ ቨርጅኒያ (Fairfax, Virginia) ውስጥ፣ እና በሴንት ጆንስ ዩኒቨርስቲ - በኑው ዮርክ፣ ኑው ዮርክ (New York, New York) ውስጥ - በመስጠት አገልግለዋል። የአንደር-ግራጅዌት ኮርሶች (undergraduate courses)ን፣ በሆፍስታር ዩኒቨርስቲ (Hofstra University)፣ በሄምፕስቴድ ኒውዮርክ (Hempstead, New York) ውስጥም አስተምረዋል።

ዶ/ር ስቶን (Dr. Stone)፣ የባችለር ኦፍ አርትስን በሳይኮሎጂ ከሳውዝ ፍሎሪዳ ዩኒቨርስቲ ያገኙ እና የማስተርስ ዲግሪ በልዩ ትምህርት (special education) በዊሊያም & ሜሪ (William & Mary) ኮሌጅ - ዋና-ትኩረታቸው በስሜታዊ መረበሾች እና የመማር እክሎች ላይ በማድረግ አግኝተዋል። በሳይኮሎጂ - ዶክትሬታቸውን በክሊኒካል እና የትምህርት ሳይኮሎጂ ከሆፍስትራ ዩኒቨርስቲ (Hofstra University) አግኝተዋል። ዶ/ር ስቶን (Dr. Stone) በተጨማሪም - በባህሪይ ምርምር-ጥናት በዶክትሬት ደረጃ ከባለሙያተኛ ፈቃድ-ጋር በቨርጅኒያ እና በኑው ዮርክ እንደ ልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ በመሆን፣ በትምህርት ቤት የስነ-ልቦና ባለሞያ (psychologist) እና ፈቃድ-ያለው የአስተዳደር-ሠራተኛ እና ተቆጣጣሪ ሆነው የቦርድ-ፈቃድ ያገኙ ናቸው።

## በበጀት-ሂደቱ ውስጥ፣ ተሳተፉ: የሕዝብ ተሰሚነት (Public Hearing) በጄንዋሪ (Jan.) 19 ይኖራል




በጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023፣ በ6:30 p.m. ላይ - የትምህርት ቤት ቦርዱ በሃሳብ-በቀረበበት የበጀት-ዓመት 2024 የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታዎች በጀት (Proposed FY 2024 Combined Funds Budget) ላይ የ'public hearing'ን የሚያካሂድ ሲሆን፣ ትኩረት የሚያደርገውም - በሠራተኞች ማካካሻ፣ አዲስ ተቋም በመክፈት፣ አዲስ ህንጻዎችን አሻሽሎ-በመስራት እና በሌሎች ትምህርት ቤት ቦታዎች ደግሞ የመጠበቂያ ጥገና በማድረግ፣ እንዲሁም ከፍ-ያለ የገንዘብ-እገዛ ከK-4 ክፍሎች ውስጥ ለማንበብና-መፃፍ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሂሳብ፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚማሩ ቦታዎችን፣ የተማሪ ማህበራዊ-ስሜታዊ እገዛ፣ የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ አገልግሎቶች፣ እና ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአትሌቲክስ የማስፋፊያ ዕቅዶች እና የተማሪ አትሌቶች እርዳታዎች ላይ - ትኩረት የሚያደግ ይሆናል።

ሃሳብ-የቀረበበት የተጣመረ የገንዘብ እርዳታ በጀቱ (The Proposed Combined Funds Budget) የሚያካትተው - የማከናወኛ በጀቱ፤ ተጨማሪ የትምህርት ቤት የአመጋገብ የገንዘብ እርዳታን፣ እንዲሁም የእርዳታ-ገቢዎች (grants) እና ልዩ ፕሮጀክቶች - አጠቃላይ መጠናቸው $359.9 ሚሊዮን የሆነ - ይህም የ4.2% ከአለፈው ዓመት ከነበረው $329.4 ሚሊዮን በጀት ከፍ-ያለ ነው።

በ'FY'2024 - የተጣመረ የገንዘብ እርዳታዎች በጀት (Combined Funds Budget) ላይ ንግግር-ማድረግ ፍላጎት ያላቸው ከሕዝብ-የተውጣጡ አባላቶች፤ በአካል-ተገኝቶ፣ ወይም በዙም (Zoom)፣ ወይም የጽሁፍ የሕዝብ አስተያየቶችን በthe online form አማካኝነት-ለማቅረብ ለመመዝገብ (sign up ለማድረግ) ይችላሉ። ከ'የተጣመረ የገንዘብ በጀት (Combined Funds Budget)' ጋር ተያያዥ-የሆኑ አስተያየቶች ብቻ የሚሰሙ-ይሆናል። ለመመዝገብ (sign up -ለማድረግ) የሚያበቃበት የመጨረሻ ቀን፣ ሮብ ጄንዋሪ (Jan.) 18 ቀን 2023 በቀትር (noon) ላይ ነው።

የ'public hearing'ን ወዲያውኑ ተከትሎ፤ ቦርዱ ሁለተኛ የተጣመረ የገንዘብ-እርዳታዎች በጀት የስራ-ክፍለ ጊዜው (Combined Funds Budget Work Session)ን ያካሂዳል። የስራ-ክፍለ ጊዜው (Work session) ላይ የተቀዳውን - በኦንላይን መመልከት ይቻላል፤ በጄንዋሪ (Jan.) 12 ቀን 2023 ላይ የተካሄደውን - የመጀመሪያውን የተጣመረ የገንዘብ እርዳታዎች የበጀት የስራ-ክፍለ ጊዜን (Combined Funds Budget Work Session) ጨምሮ - መመልከት ይቻላል።

ሃሳብ-የቀረበበት የFY 2024 የተጣመረ የገንዘብ እርዳታ በጀቱ (The Proposed FY 2024 Combined Funds Budget) እና ሙሉ የበጀት የጊዜ-አቀማመጥ - በACPS የበጀት/Budget ድህረ-ገጽ ላይ ለምልከታ-የሚገኝ ይሆናል። በልዩ-ሁኔታ የተጠራውን ስብሰባ ለመመልከት ወይም የበጀት የስራ ክፍል (Work Session)ን በቀጥታ-ስርጭት በዙም (Zoom) አማካኝነት ለመመልከት መመዝገብ ወይም በትምህርት ቤት ቦርድ ድህረ-ገጽ ላይ ተመልከቱ።

## የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ቤተሰቦች፤ መረበሽን እና ጭንቀትን በመቆጣጠር ላይ ለመወያት - ጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023፣ ተጋብዘዋል




ለሚቀጥለው የ'Youth Speak Up' ዝግጅት የሚካሄድበትን - ሐሙስ ጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023ን፣ ከ6-8 p.m. በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት (1005 Mt Vernon Ave.) - በቀን-መቁጠሪያ ካላንደራችሁ ላይ መስግቡት። ይህ ዝግጅት፤ ስለ መረበሽ እና ጭንቀት ቁጥጥር ጤናማ-የሆኑ መንገዶች ለመወያየት፣ የመካከለኛ (middle) ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን እና ወላጆቻቸውን በአንድነት-አብሮ የሚያሳትፍ-ዝግጅት ነው።

ዝግጅቱ - በአሌክሳንድርያ አደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ መጠቀም መከላከያ ቅንጅት (Substance Abuse Prevention Coalition of Alexandria)፣ በ'Children Youth and Families Collaborative Commission'፣ በአሌክሳንድርያ በጉርምስና ላይ ላሉ የእርግዝና ዘመቻ (Alexandria Campaign on Adolescent Pregnancy)፣ በ'Gang Prevention Community Task Force' እና በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) የሚዘጋጅ-ይሆናል። በቅርብ-

ጊዜ ተደርጎ-የነበረው ‘Youth Speak Up’ ዝግጅት - በዲሴምበር (December) 2021 ላይ ተዘጋጅቶ-የነበረ ሲሆን፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ተማሪዎች ከወረርሽኙ በኋላ ሕይወትን እንዴት መምራት እንደሚያስፈልጋቸው አጉልተው-ያሳዩበት የፓኔል (panel) ዝግጅት-ነበር።
የማስተርጎም አገልግሎቶች፤ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ በአረብኛ እና በዳሪ ቋንቋዎች ይቀርባል። ለተጨማሪ መረጃዎች እና መገኘታችሁን-ለመግለጽ (RSVP ለማድረግ) ‘ParentSquare’ን ጎብኙ።

## የጀንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በጀንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 ስብሰባው ላይ፣ ከጀምስ ኬ. ፖልክ (James K. Polk) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሠራተኞች እና ተማሪዎች በሚደረገው ጉብኝት - እና ከአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) መዘምራን (choir) በሚቀርበው ዝግጅት፤ የትምህርት ቤት ቦርዱ አስደሳች-ጊዜ የሚኖረው ይሆናል። ቦርዱ በተጨማሪም - የሁለተኛ አጋማሽ የACPS የ‘Vision, Integrity and Passion (VIP)’ ተቀጣሪ-ሠራተኞችን እውቅና-የመስጠት ሽልማቶች አሸናፊዎችን - እንኳን-ደስ አላችሁ ይላል።

የስብሰባው አጀንዳ - በFY 2024 Combined Funds budget’ ላይ የሚኖረውን የ‘public hearing’ን የሚያካትት፣ እና በተጨማሪም የሚከተሉት ርዕሶችን ይመለከታል:

- የአድቫይዘሪ ኮሚቴ - አዲስና-ማሻሻያ (update)።
- ከትምህርት ቤት እና የሕግ-አስከባሪነት አባርነት (School and Law Enforcement Partnership (SLEP) የቀረቡ የምክር-አስተያየቶች።
- የ‘ተሰጥዖ እና ስጦታ ያላቸው (Talented and Gifted (TAG)’ አዲስና-ማሻሻያ (update)።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ። በ‘public hearing’ ላይ ለመናገር - ለመመዝገብ (sign up ለማድረግ)፤ እባካችሁ በኦንላይን ተመዝገቡ (sign up አድርጉ)።

# በጀንዋሪ (Jan.) 5 ቀን 2023 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ጀንዋሪ (Jan.) 5 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 131.1 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ [Alexandria COVID-19 dashboard] ጎብኙ።

የመረጃ-ስብሰቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በጀንዋሪ (Jan.) 5 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።